የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

፴፪ኛ ዓመት ቁጥር ፳፬
አዲስ አበባ ሚያዝያ ፳ ቀን ፪ሺ፲፰

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32nd Year No. 24
ADDIS ABABA, 28th April, 2026

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፯/፪ሺ፲፰

ለብሔራዊ የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ሥርዓት ማስፋፊያ ፕሮጀክት የሚውል ተጨማሪ ብድር ከኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ……………...............ገጽ ፲፱ሺ፮፻፷፫

## Content

Proclamation No. 1407/2026

Export –Import Bank of Korea Additional Loan Agreement for Southern Extension of the National Electricity Grid Power Transmission Project Ratification Proclamation ………………………......................Page 19663

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፯/፪ሺ፲፰**

**<u>በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ</u>**

ለብሔራዊ የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ሥርዓት ማስፋፊያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፴ ሚሊዮን ፪፻፳፫ ሺህ የአሜሪካን ዶላር (ስልሳ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሃያ ሶስት ሺህ የአሜሪካን ዶላር) ተጨማሪ ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል ጥቅምት ፲፬ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፲፭ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም ባካሄደው ፲፪ኛ መደበኛ ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

**PROCLAMATION NO. 1407/2026**

**<u>A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND EXPORT-IMPORT BANK OF KOREA</u>**

**WHEREAS**, the Loan Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and Export –Import Bank of Korea stipulating that Export –Import Bank of Korea shall provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia an Additional Loan in an amount equivalent to Sixty Million Two Hundred Twenty Three Thousand United States Dollar (USD 60,223,000) for financing Southern Extension of the National Electricity Grid Power Transmission Project was signed on the 24th day of October 2025;

**WHEREAS**, the house of peoples Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified this agreement at its 12th regular session held on 24th day of March 2026;

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለብሔራዊ የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ሥርዓት ማስፋፊያ ፕሮጀክት የሚውል ተጨማሪ ብድር ከኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፯/፪ሺ፲፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል ጥቅምት ፲፬ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም የተፈረመው EDCF LOAN AGREEMENT NO. ETH.12 በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፷ ሚሊዮን ፪፻፳፫ ሺህ የአሜሪካን ዶላር (ስልሳ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሃያ ሶስት ሺህ የአሜሪካን ዶላር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሚያዝያ ፳ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም**

**ታዬ አፅቀስላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**NOW, THERFORE**, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "Export –Import Bank of Korea Additional Loan Agreement for Southern Extension of the National Electricity Grid Power Transmission Project Ratification Proclamation No. 1407/2026".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement EDCF LOAN AGREEMENT NO. ETH.12 signed on the 24th day of October 2025 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and Export – Import Bank of Korea is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance</u>**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan an amount equivalent to Sixty Million Two Hundred Twenty Three Thousand United States Dollar (USD 60,223,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force upon its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 28th day of April 2026**

**TAYE ATSKESELASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDRAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**